# የታሰሩትስ አቶ መለስ ናቸዉ - በክፋትና በጭካኔ !



ግርማ ካሳ (muziky68@yahoo.com)
ሐምሌ 28 ቀን 2001

ሁለቱም በኢትዮጵያ እየተፋፈመ በመጣዉ የፖለቲካ ሂደት ዉስጥ ትልቅ ስፋራ አላቸዉ። ሁለቱም አባል የሆኑበት ደርጅት ሊቀመንበር ናቸው። ሁለቱም በደጋፊዎቻቸዉ ይደነቃሉ። ሁለቱም የሁለተኛ ደረጅ ተማሪ የነበሩ ጊዜ ጎበዝ ተማሪዎች ነበሩ። ሁለቱም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሆነዋል። ሁለቱም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸዉን ያጠናቀቁት በአዲስ አበባ ነው። ሁለቱም ወላጆች እንደመሆናቸዉ የልጅን ፍቅር ያውቃሉ። ሁለቱም ኢትዮጵያዉያን ናቸው።

የመጀመሪው አቶ መለስ ዜናዊ ይባላሉ። የአምሳ አራት አመት አዛዉንት ናቸዉ። እናታቸዉ የአዲቋላ (ኤርትራ ተወላጅ) ሲሆኑ አባታችዉ ደግሞ የአድዋ ትግራይ ሰው ነበሩ። ሌላኛዋ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ናቸው። አባታቸው የወለጋ ሰው ሲሆኑ እናታቸዉ ደግሞ የሸዋ ሰው ናቸዉ።

በነዚህ ሁለት የፖለቲካ ሰዎች ዉስጥ ትግራይ፣ ኤርትራ፣ ወለጋና ሸዋን እናያለን። (ከቀድሞ የኢትዮጵያ አሥራ አራቱ ክፍለ ሃገራት አራቱ ማለት ነዉ)

አቶ መለስ ወላጆቻቸው ያወጡላቸዉ ስም ለገሰ የሚል ነበር። «ዜናዊ» ማለት ዜና አብሳሪ ማለት ይመስለኛል። ወላጆቻቸዉ ለገሰ ዜናዊ ሲሏቸዉ «የሚያበስር ተሰጠን፣ ተወለደልን፣ ተለገሰን» ብለው ሳይሆን አይቀርም ። መቼም ወላጆቻቸው ያኔ የተመኙት አቶ መለስ(ለገሰ) መልካም ብሥራት፣ መልካም ወሬ እንዲያብሰሩ ይመስለኛል።

ወደ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ስንመለስ ወላጆቻቸዉ «ያማረች፣ የጣፈጠች፣ በሰዉ የተወደደች ትሁን» ብለዉ ይመስላል ብርቱካን ያሏቸዉ። «ሚደቅሳ»ም ተመሳሳይ ትርጉም አለዉ። «ሚደቅሳ» በኦሮምኛ ማሳመር፣ ማስዋብ ማለት ነዉ።

የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳም ሆነ የአቶ መለስ ዜናዊ ቤተሰቦች ሁለቱም ልጆቻቸዉ ትልቅ ደረጃ ደርሰዉ፣ መልካም ነገር አድርገዉና በመልካም ነገር ታዉቀዉ እንዲያልፉ ፍላጎት እንደነበራቸዉ ነዉ እንግዲህ የምናየዉ።

የነዚህ ሰዎች መመሳሰል እዚህ ላይ ያበቃል። አሁን ባለንበት ሁኔታ አቶ መለስ ዜናዊ ትልቅ ጭካኔ የተሞላበት ኢሰብአዊ ሥራ በሰላማዊ ዜጎች ላይ እስኪሰሩ ድረስ በጥላቻና በክፋት የተሞሉ እልኸኛ ሰዉ እንደሆኑ እያሳዩ ናቸዉ።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ «ቅንጅት የሰዉ ጠላት የለዉም። ወያኔ ጠላት አይደለም። ለአገራችን መፍትሄ ፍቅር ነዉ። ያሰሩኝን ይቅር ብያለሁ» እስከማለት ድረስ በፍቅርና በደግነት የተሞሉ፣ የበደሏቸዉንና ወደ ሁለት አመት ገደማ በግፍ ያሰሯቸዉን ሰዎች ይቅር ያሉ ታላቅ ሰዉ ናቸዉ። አንድ ልዩነት በሉልኝ።

አቶ መለስ ዜናዊ በሚቆጣጠሩት የደህንነት ጽ/ቤት፣ የፌደራል ፖሊስና የአጋዚ ጦር ይመካሉ። እነዚህን ሕሊና የለሽ ሰዎች በመላክ፣ በሙቶ የሚቆጠሩ ዜጎችን በጠራራ ጸሃይ አስገድለዋል። በሙቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያንን በግፍ አሳስረዋል። ሰላማዊ መንደሮችን እንዲቃጠሉ አስደርገዋል።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የታጠቀ ሰራዊት የላቸዉም። በቤታቸዉ መሳሪያ አልተገኘም። በእጆቻቸዉ የወደቀዉን ያነሳሉ እንጂ የቆመዉን ተኩሰዉ አይጥሉም። የሚተማመኑት በሕዝብ ጉልበት እንጂ በጠመንጃ አይደለም። ሁለተኛ ልዩነት በሉልኝ።

አቶ መለስ ዜናዊ በተደጋጋሚ እርሳቸዉንና ደጋፊዎቻቸዉን ትዝብት ዉስጥ እስኪከቱ ድረስ የሚዋሹ ሰዉ ናቸዉ። ለምስሌ የቅንጅት መሪዎች ከሁለት አመታት በፊት በተፈቱ ጊዜ አቶ መለስ « ከአሁን በኋላ ወደ ፊት እንጂ ወደ ኋላ መመለስ የለብንም። ሕግን እስካልጣሱ ድረስ (የተፈቱት እሥረኞች) ሙሉ የፖለቲካ መብታቸዉ ተጠብቆ መንቀሳቀስ ይችላሉ» ነበር ያሉት። ነገር ግን ታሪካቸዉን ለዉጠዉ፣ የተናገሩትን አጥፈዉ፣ ቀድሞ ከተፈቱት እሥረኞች መካከል ወ/ት ብርትካን ሚደቅሳ በግፍ እንድትታሰር ፈቅደዋል።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ያላደረጉትን «አድርጊያለሁ» እንዲሉ፣ እንዲዋሹ ግፊትና ዛቻ ቢደረግባቸዉም «እምቢ» ብለዉ ለእዉነት የቆሙ ሰዉ ናቸዉ። ለእዉነትም በመቆማቸዉ ትልቅ ዋጋ በአሁኑ ወቅት በመክፈል ላይ ይገኛሉ። ሶስተኛ ልዩነት በሉልኝ።

አቶ መለስ ዜናዊ ከቀድሞ የ66ቱ አብዮት ዘመን ከነበረዉ፣ እርስ በርስ በደም ከተቃባዉ ፣ እምነተ ቢስ ፍልስፍናን ለኢትዮጵያ ህዝብ ካስተዋወቀዉ፣ አገራችንን ወደ ጨለማ ከወሰደዉ ትዉልድ ናቸዉ። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በጥላቻና በቂም በቀል ካልተሞላዉ ከአዲሱ ትዉልድ ናቸዉ። አራተኛ ልዩነት በሉልኝ !

ምንም ቢሆን፣ ክፉ የሰራ ሰዉ በመንፈሱ ሰላም ስለማያገኝ ፣ አቶ መለስ ዜናዊ የጭንቀትና የመንፈስ ረብሻ፣ የፍርሃት እሥረኛ ሆነዉ እየተሰቃዩ ናቸዉ። እራሳቸውን ይፈራሉ። አብረዋቸዉ ያሉትን የፖሊት ቢሮ አባላት ይፈራሉ። ህዝቡን ይፈራሉ። (ምናልባት የማይፈሩት ጎርደን ብራዉንና ሲልቪዮ ቤሎስኮኒን ብቻ ሳይሆን አይቀርም።) ሌሊት፣ በቤተ መንግስትም በላጠጠ መኝታ ላይ እየተኙ እንቅልፍ የላቸዉም። ለዚህ ሳይሆን አይቀርም ነገሮችን ለመርሳት ያስችል ዘንድ ሲጋራና ጫት አረቄና ካቲካላ የአራት ኪሎን ቤተ መንግስት የሞላዉ። አላወቁትም እንጂ የታሰሩትስ አቶ መለስ ዜናዊ እራሳቸዉ ናቸዉ ። በክፋትና በጭካኔ !

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በመንፈሳቸዉ ነጻ የሆኑ ሴት ናቸዉ። በሥጋ በማይመች ቦታ ታስረዋል። ግን በዚያ በማይመች ቦታ ሆነው የጣፈጠ እንቅልፍ ይተኛሉ። ዉስጣቸዉ በፍርሃት የተሞላ አይደለም። በራሳቸዉ ይተማመናሉ። ከማንም ጋር መኖር ይችላሉ። በየትም ቦታ ቢሄዱ ማንም አይነካቸዉ።አምስተኛ ልዩነት በሉልኝ!

አቶ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያዉያንን በሚያዩበት ጊዜ መጀመሪያ የሚያዩት ትግሬነትን ወይንም አማራነትን ወይንም ኦሮሞነትን ነው። አገሪቷን በዘር ላይ በተመሰረተ ፌደራል አወቃቀር ነዉ ያካለሏት። ሕዝብ በዘሩ እንዲከፋፈል፣ አንዱ ጎሳ በአንዱ ጎሳ ላይ እንዲነሳ የሚገፋፋ ፖለቲካን ነው ለመዘርጋት የሞከሩት። ትዝ ይለኛል አንድ ቀን በፓርላማ ካቢኔዎቻቸዉን ሲያስተዋዉቁ። «አቶ ጁነዲን ሳዶ - ብሄር ኦሮሞ፣ አቶ አዲሱ ለገሰ ብሄር አማራ ፣ አቶ ስዩም መስፍን - ብሄር ትግሬ » እያሉ ነበር ያስተዋወቁት።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ግን መጀመሪያ የሚመለከቱት ኢትዮጵያዊነትን ነዉ። በሁለተኛነት የሚመለከቱት ኢትዮጵያዊነትን ነዉ። በሶስተኛነት የሚመለከቱት ኢትዮጵያዊነትን ነዉ።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የሚመሩት ደርጅት፣ አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ፣ እንደብሄር መብት ያሉ የቡድን መብቶች መከበር አለባቸዉ ብሎ ቢያምንም፣ የሁሉም ነገር ምሰሶ አደርጎ የሚቀበለዉ ግን የግለሰብ መብት መከበርን ነዉ።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የብሄር ድርጅቶች የነበሩትን፣ በብሄር ከመከፋፈል ይልቅ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር እንዲሰባሰቡ ትልቅ ጥረት ያደረጉ ሴት ናቸዉ። የአንድነት ፓርቲ ሕጋዊነቱን ከማግኘቱ በፊት ሁሉ የተለያዩ የጎሳ ድርጅቶች፣ በተናጥልና በጎሳቸዉ ሥር ከመሰባሰብ ይልቅ ለጋራ ጥቅም፣ ለእኩልነት፣ ለፍትህ በኢትዮጵያነት ሥር እንዲሰባሰቡ የሚያደርገዉ መድረክ የተሰኘዉ አካል ተግባራዊ እንዲሆን ከፍተኛ ሚና ዉስጥ ዉስጡን ከተጫወቱት ቁልፍ ሰዎች ዉስጥ ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳ በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ናቸዉ።

የእነ አቶ መለስ ዜናዊ ፖለቲካ፣ እየለጠጠና እያሰፋ ያለዉን የዘር መከፋፈል፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እያቀራረቡትና እያሰባሰቡት ነዉ። አቶ መለስ ዜናዊ የቀድሞ ጓደኛቸዉን አቶ ሲዬ አብርሃን ሲያዩ ትግሬዉ ሲዬ አብርሃ ነዉ የሚያዩት። የቀድሞ ፕሬዘዳንት ዶር ነጋሶ ጊዳዳን ሲያዩ ኦሮሞዉ ነጋሶን ነዉ የሚያዩት። ዶር በየነ ጴጥሮስን ሲያዩ ሃዲያዉ በየነን ነዉ የሚያዩት። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ግን ኢትዮጵያዊዉን ስዬ አብርሃ፣ ኢትዮጵያዊዉን ነጋሶ ጊዳዳ፣ ኢትዮጵያዊዉን በየነ ጴጥርስን ነዉ የሚያዩት።ይህ ትልቁና ስድስተኛ ልዩነታቸዉ ነዉ።